# አዲስ ነጋሪ ጋዜጣ

# ADDIS NEGARI GAZETA

OF THE CITY GOVERNMENT OF ADDIS ABABA

| አራተኛ ዓመት ቁጥር ፶፮<br>አዲስ አበባ-ሚያዝያ ፳፮ ቀን ፲፱፻፺፰ ዓ.ም. | በአዲስ አበባ ከተማ ጊዜያዊ<br>አስተዳደር ጠባቂነት የወጣ | 4th Year No. 56<br>ADDIS ABABA- 4th May, 2006 |
|---|---|---|


## ማውጫ


ደንብ ቁጥር ፳፭/፪ሺ.ህ
የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የአካባቢ ብክለት ቁጥጥር ደንብ ........................................ ገጽ ፰፻፹፰


## CONTENTS


Regulation No. 25/2007
Addis Ababa City Government Environmental Pollution Control Regulations .............................. Page 888


## ደንብ ቁጥር ፳፭/፪ሺ.ህ

## የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የአካባቢ ብክለት ቁጥጥር ደንብ

አንዳንድ ማሕበራዊና ኢኮኖሚያዊ የልማት እንቅስቃሴዎች ልማቱን የሚቀለብስ ጎጂ አካባቢያዊ ተጽዕኖ ሊያስከትሉ የሚችሉ በመሆናቸው፡፡

አካባቢን መጠበቅ በተለይም የሰውን ጤንነትና በጎ ሁኔታ እንደዚሁም የሕያዋያን ደህንነትና የተፈጥሮ ስነ ውበት ማቆየት የሁሉም ተግባርና ኃላፊነት በመሆኑ፤

የመከላከያ ወይም የማገጃ እርምጃዎች በመውሰድ በማህበራዊና በኢኮኖሚያዊ ልማት እንቅስቃሴዎች የሚከሰተውንና የማይፈለገውን ብክለት ማስወገድና መከላከል ተገቢ በመሆኑ፤

የአዲስ አበባ ከተማ ጊዜያዊ አስተዳደር በተሻሻለው በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ቻርተር አዋጅ ቁጥር ፫፻፷፩/፲፱፻፺፭ አንቀጽ ፷፮/፪ እና በአዋጅ ቁጥር ፲፯/፲፱፻፺፮ አንቀጽ ፳፱ ንዑስ አንቀጽ ፪ /ረ/ መሠረት ይህን ደንብ አውጥቷል፡፡

### ክፍል አንድ
### ጠቅላላ

፩. አጭር ርዕስ

ይህ ደንብ «የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የአካባቢ ብክለት ቁጥጥር ደንብ ቁጥር ፳፭/፪ሺ.ህ ዓ.ም» ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

፪. ትርጓሜ

የቃሉ አገባብ የተለየ ትርጉም የሚያሰጠው ካልሆነ በስተቀር በዚህ ደንብ ውስጥ፣

፩. «አስተዳደር» ማለት የአዲስ አበባ ከተማ ጊዜያዊ አስተዳደር ነው፡፡

፪. «ባለስልጣን» ማለት የአዲስ አበባ ከተማ ጊዜያዊ አስተዳደር የአካባቢ ጥበቃ ባለሥልጣን ነው፡፡

*REGULATION No 25/2007*
*ADDIS ABABA CITY GOVERNMENT ENVIRONMENTAL POLLUTION CONTROL REGULATIONS*

Whereas, some so social and economic development endeavors may inflict environmental harm that could make the endeavors counter-productive;

Whereas, the protection of the environment, the safe guarding of human health and well being, as well as the maintaining of the living tings and aesthetic value of nature, in particular are the duty and responsibility of all;

Whereas, it is appropriate to eliminate or to mitigate pollution as an undesirable consequences on social and economic development activities.

Nowtherefore, in accordance with article 66/2 of Addis Ababa city government revised charter proclamation No. 361/2003 and article 29/2/F/ of the city master plan preparation, issuance and implementation proclamation No. 17/2004, the provisional government of Addis Ababa city here by issued this regulations as follows:-

### *Part One*
### *General*

1. ***Short Title***
   These regulations may be cited as "Addis Ababa City Government Environmental Pollution Control Regulation No.25/2007"

2. ***Definitions***
   Unless the context requires otherwise; in these regulations.
   1. "Government" means Addis Ababa city provisional Government
   2. "Authority" means the Addis Ababa city Government Environmental protection Authority.


ያንዱ ዋጋ
Unite Price 15.50

አዲስ ነጋሪ ጋዜጣ ፖ.ሣ.ቁ. ፪ሺ፬፻፵፭
Addis Negarit Gazeta P.O. Box 2445

፫. «አካባቢ» ማለት በመሬት፣ በአካባቢ አየር፣ በአየር ሁኔታ እና በአየር ንብረት፣ በውሃ፣ በህያውያን፣ በድምጽ፣ በሽታ፣ በጣእም፣ በማህበራዊ ጉዳዮች እና በስነ ውበት ሳይወሰን በተፈጥሮአዊ ሁኔታዎች ወይም በሰው አማካኝነት ተሻሽለው ወይም ተለውጠው የሚገኙ ነገሮች በጠቅላላ ያሉበት ቦታ፣ እንዲሁም መጠናቸው ወይም ሁኔታቸው፣ የሰው ወይም የሌሎች ሕያዋን በጎ ሁኔታን የሚነኩ መስተጋብሮቻቸው ድምር ነው፡፡

፬. «ብክለት» ማለት በዚህ ደንብ ወይም አግባብ ባለው ሌላ ሕግ የተደነገገን ማንኛውንም ግዴታ፣ ማዕቀብ ወይም ገደብ ጥሶ የማንኛውንም አካባቢ ክፍል ቁሳዊ፣ ጨረራዊ፣ ሙቀታዊ፣ ንጥረ ነገራዊ፣ ሥነ-ሕይወታዊ ወይም ሌላ ባሕርይን በመለወጥ የተፈጠረ፣ በሰው ጤና ወይም በጎነት ወይም ደግሞ በሌሎች ሕያውያን ላይ አደገኛ የሆነ ወይም አደገኛ ሊሆን የሚችል ሁኔታ ነው፡ :

፭. «ኬሚካል» ማለት ኤለመንት ወይም ያልተቀላቀለም ይሁን የተቀላቀለ ውሁድ፣ ወይም ተቀምሞ በሰው የተሰራ ወይም ደግሞ ከተፈጥሮ የተገኘ ቁስ አካል ነው፡፡

፮. «አየር» ማለት ተፈጥሮአዊ የሆነ የተለያዩ ጋዞች ቅልቅል ሲሆን በዚህ ደንብ ውስጥ ከመኖሪያ ቤት ውጭ ያለው አየር በሥራ ቦታ ሕዝባዊ ግልጋሎት የሚሰጥበት ቦታ ያለው አየር ነው፡፡

፯. «አደገኛ ነገር» ማለት በሰው ጤና ወይም በአካባቢ ላይ ጉዳት የሚያደርስ ጠጣር፣ ፈሳሽ ወይም ጋዝ ወይም ተክል፣ እንስሳ ወይም ረቂቅ ህዋስ ነው፡፡

፰. «አደገኛ ቆሻሻ» ማለት ተፈላጊነት የሌለው ሆኖ በአካባቢ ወይም በሰው ደህንነት ወይም ጤና ላይ ጉዳት ያደርሳል ተብሎ የሚታመን ማንኛውም ነገር ነው፡፡

፱. «ደረጃ» ማለት የአካባቢ የጥራት ወይም የብክለት መጠን መለኪያ መስፈርት ነው፡፡

፲. «ፈቃድ» ማለት በዚህ ደንብ መሠረት በጽሑፍ የሚሰጥ የብክለት ቁጥጥር ፈቃድ ነው፡፡

፲፩. «የአካባቢ ብክለት» ማለት በአካባቢ ተፈጥሮአዊ ሁኔታ ላይ ለውጥ በማስከተል በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ በሕይወት፣ በግንባታዎች፣ ወይም በሰው ልጅ ተለምዶአዊ ኑሮ ላይ ጉዳት ማድረስ ነው፡፡

፲፪. «በካይ» ማለት ፈሳሽ፣ ጠጣር ወይም ጋዝ የሆነ በቀጥታም ሆነ ቀጥተኛ ባልሆነ መንገድ፡-

ሀ) ያረፈበትን የአካባቢ ክፍል ጥራት በመለወጥ ጠቀሜታ የመስጠት አቅሙን የሚያጓድል፣ ወይም

ለ) በሰው ጤና ወይም በሌሎች ህያዋን ላይ ጉዳት የሚያደርስ ወይም ሊደርስ የሚችል መርዝን፣ ክርፋትን፣ ጨረርን፣ ድምፅን፣ ንዝረትን፣ ሙቀትን ወይም ሌላ ክስተትን የሚያመነጭ ማንኛውም ነገር ነው፡፡

፲፫. «ውሃ» ማለት የገጸ ምድርና የከርስ ምድር ውሃ ነው

፲፬. «መልቀቅ» ማለት በውል ታስቦም ይሁን ሳይታሰብ በካይን ወደ ማንኛውም የአካባቢ ክፍል መጨመር ነው፡፡

3. "Environment" means the totality of all materials whereas in their natural state or modified or changed by human beings, their external spaces and the interactions which affect their quality or quantity and the welfare of human or other living things, including but not restricted to land, atmosphere, weather and climate, water, living things, sound, odor, taste social factor and aesthetics

4. "pollution" means any condition which is hazardous or potentially hazardous to human health, safety, or welfare or to living things created by altering any physical, radioactive, thermal, chemical, biological or other property of any part of the environment in contravention of any condition. Limitation or restriction made under these regulations and any other relevant laws.

5. "Chemical" means an element or a compound whether by itself, or in a mixture or a preparation, whether manufactured or obtained from nature.

6. "Air" in these regulations means the natural mixture of gases that are found out of home and include in areas where work is done.

7. "Hazardous material" means any substance in solid, liquid or gaseous state, or any plant, animal or micro organism that is injurious to human health or the environment.

8. "Hazardous waste" means any unwanted material that is believed to be deleterious to human safety or health or the environment.

9. "Standard" means the measurement of environmental quality or environmental pollution.

10. "License" means a written permit of pollution control issued pursuant to these regulations.

11. "Environmental pollution" means any change in the natural environment that directly or indirectly affect the life, construction, or day to day activities of human being.

12. "Pollutant" means any substance whether liquid, solid, or gas which directly or indirectly.

(a) Alters the quality of any part of the receiving environment so as to affect its beneficial use adversely; or

(b) Produce toxic substances, diseases, objectionable odor, radioactive, noise, vibrations, heat or any other phenomenon that is hazardous or potentially hazardous to human health or to other living things.

13. "Water" means both surface and ground water.

14. "Release" means disposing of any pollutant in the environment in any way be it intentionally or otherwise.

፲፭. «ፍሳሽ» ማለት ተጣርቶ ወይም ሳይጣራ በቀጥታ ወይም ቀጥተኛ ባልሆነ መንገድ ወደ አካባቢ የሚለቀቅ ቆሻሻ ውሃ ወይም ሌላ ቆሻሻ ፈሳሽ ነው።

፲፮. «የአካባቢ ተቆጣጣሪ ወይም ተቆጣጣሪዎች» ማለት በዚህ ደንብ አንቀጽ ፲፪ መሠረት የሚሰየም አካል ነው።

፲፯. «ሰው» ማለት የተፈጥሮ ሰው ወይም በሕግ የሰውነት መብት የተሰጠው አካል ነው።

፫. የደንቡ ተፈጻሚነት ወሰን

፩. ይህ ደንብ አደገኛ ነገር እና በካዮችን በማመንጨት ወይም በማውጣት በአካባቢ ደህንነት ላይ ብክለት እና አሉታዊ ተፅዕኖዎችን ሊያስከትሉ ይችላሉ ተብለው በሚገመቱ ፋብሪካዎች የንግድ፣ የትምህርት፣ የጤና ተቋማት፣ ኢንዱስትሪዎች፣ ሌሎች ደርጅቶች፣ መኖሪያ ቤቶችና መሰል የሰው ልጅ ተግባራት እና በካዩ ላይ ተፈጻሚ ይሆናል።

፪. ደንቡ ከመውጣቱ በፊት በጸደቁ ፕሮጀክቶችና በተቋቋሙ ድርጅቶች ላይም ይህ ደንብ ተፈጻሚነት ይኖረዋል። ዝርዝሩ ባለሥልጣኑ በሚያወጣው የአፈጻጸም መመሪያ ይወሰናል።

፬. ዓላማ

ደንቡ የሚከተሉት ዓላማዎች ይኖሩታል።

፩. አካባቢን ከማናቸውም ብክለት መጠበቅ፣ ወይም መከላከል፣

፪. የአገሪቱ የእድገት ደረጃ እና አቅም በሚፈቅደው መጠን በአስተዳደሩ ውስጥ ብክለትን መከላከልና በረጅም ጊዜ ማስወገድ የሚቻልበትን ሁኔታ መቀየስ፣

፫. ማንኛውም ተግባር ብክለት የሚያስከትል መሆን አለመሆኑ በቅድሚያ እየተጣራ እንዲካሄድ እና ብክለት በሚደርስበት ጊዜም የበለጠ ጉዳት ከመድረሱ በፊት መፍታት የሚቻልበትን ሁኔታ ማመቻቸት።

፬. በብክለት ምክንያት የደረሰውን ጉዳት በካዩ ወደቀድሞው ሁኔታ የሚመልስበትንና ለድርጊቱ ተጠያቂ የሚሆንበትን ሥርዓት መዘርጋት፣

፭. በአካባቢ ላይ ብክለት የማያስከትሉ ቴክኖሎጂዎችን መጠቀምን የሚያበረታታና ብክለትን ለማስወገድ የሚረዱ ፈጠራዎችን ማገዝ።

፮. በፌዴራሉ መንግሥት ስለ አካባቢ ብክለት ቁጥጥር የወጣው አዋጅ ቁጥር ፫፻/፲፱፻፺፬ እና የአስተዳደሩ የአካባቢ ፖሊሲዎችና ስትራቴጂዎች ተፈጻሚ የሚሆኑበትን ምቹና ህጋዊ ሁኔታ መፍጠር።

ክፍል ሁለት

ስለ አካባቢ ደረጃዎች እና ብክለት ቁጥጥር

፭. ስለ አካባቢ ደረጃዎች

፩. የአካባቢ ደረጃዎች፣ በጥራት ደረጃ፣ በቆሻሻ ማስወገድ ደረጃ፣ ወደ አየር በሚለቀቁ በካይ ነገሮች ደረጃ፣ በአደገኛ ነገሮች የአመራረት እና አያያዝ ሂደቶች ደረጃ እና በመሳሰሉት ይገልጻሉ።



15. "Effluent" means waste water, other fluid, treated or untreated, discharged directly or indirectly in to the environment.

16. "Environmental inspector or inspectors" means the body designated under article 12 of these regulations.

17. "Person" means natural person or juridical person.

*3. Scope of application*

1. These regulations shall be applicable to factories, commercial enterprises, educational centers, health institutions, industries, other enterprises, home & similar human activities and on polluters which generate & extracts hazardous material & on pollutant which is belived to harm & bring about negative impact over the environment.
2. These regulations shall be applicable to approved projects and established enterprises prior to the issuance of these regulations. The details will be determined through directives to be issued by the authority.

*4. Objectives*

These regulations has the following objectives to:-

1. Safeguarding or protecting the environment from any pollution.
2. Design the condition to protect pollution and avoid it in the long run taking in to account the development & the capacity of the country.
3. Render any activity with prior investigation whether or not it may pollute the environment and to adjust conditions in case where pollution sustained for severe materialize damage.
4. Design a system as to how a pollutant reinstate the polluted to its original position and made him responsible for his activity for the damage caused as result of pollution.
5. Keep and encourage the adoption of technologies free from pollution and creativities to eliminate pollution.
6. Establish favorable & legal conditions for the implementation of environmental pollution control proclamation No 300/2002 enacted by Federal Government as well as land Environmental policies and strategies of the Administration.

Part-Two

Environmental Standards & control of pollution

*5. Environmental Standards*

1. Environmental Standards are explained by quality standards, standards of waste disposal, standards of pollutants releases in to air, standards of production & control of hazardous materials and the like.

4

፪. አስተዳደሩ የራሱን የአካባቢ ደረጃዎች እስኪያወጣ በፌዴራል መንግሥቱ አግባብነት በአላቸው መስሪያ ቤቶች የወጡ የአካባቢ ደረጃዎችን፣ ይህ ባልወጣበት ሁኔታ ደግሞ አግባብነት ባላቸው ዓለም አቀፍ ድርጅቶች የወጡ የአካባቢ ደረጃዎችን እንደ አግባብነታቸው መከበራቸውን ባለሥልጣኑ ይቆጣጠራል፡፡

፮. <u>ስለ ጥራት ደረጃ</u>

፩. አስተዳደሩ በዚህ ደንብ አንቀጽ ፭ በተደነገገው መሠረት የጥራት ደረጃዎችን ለመወሰን ከዚህ በታች የተዘረዘሩትን መሠረት ያደርጋል፡፡

ሀ) ለሰው ልጅ ጤንነት ለአካባቢ ደህንነት እንዲሁም ለልዩ ልዩ አገልግሎቶች የሚውል አግባብ ያለው የውሃ ጥራት ደረጃ፣

ለ) ለሰው ልጅ ሕይወትና ጤንነት፣ ለእንስሳትና ለተክሎች ደህንነትና እርባታ ተስማሚ የሆነ የአየር ጥራት ደረጃ እና ወደ አየር የሚለቀቁ ነገሮች ደረጃ፣

ሐ) ወደ አፈር የሚጨመሩ ኬሚካሎች ዓይነትና መጠን የሚወስኑ የአፈር ደህንነትን የሚጠብቅ የአፈር ጥራት ደረጃ፣

መ) ለኢንዱስትሪ፣ ለግንባታ ቦታዎች፣ ለተሽከርካሪዎች ለአውሮፕላኖች ለልዩ ልዩ መሳሪያዎች፣ ለንግድ ተቋማትና ለሌሎች ድምጽ አመንጭ ነገሮች የድምጹ መጠን ደረጃ፣

ሠ) የአደገኛ ነገሮች አመራረትና አያያዝ ደረጃ፣

ረ) ወደ ውሃ አካላትና ወደ ፍሳሽ መስመሮች የሚለቀቁ የፍሳሽ ደረጃ፣

ሰ). ለአካባቢ ደህንነት እና ለሰው ልጅ ጤንነት የሚስማማ የሽታ መጠን ደረጃ፣

፪. የውሃ ጥራት ደረጃ ለቤት ውስጥ አገልግሎት፣ ለኢንዱስትሪ፣ ለመዝናኛ እና እንደ አስፈላጊነቱ ለሌሎች ተግባሮች ጥቅም ላይ የሚውል ውሃን የሚመለከት ይሆናል፡፡

፫. የአየር ጥራት ደረጃ

ሀ) ለሰው ልጅ ሕይወት ጤንነት እና ደህንነት አስፈላጊ የሆነ ዝቅተኛ የአየር ጥራት ደረጃን፣

ለ) በሰው ልጅ ጤንነትና ሕይወት፣ በእንስሳትና በተክሎች ደህንነት እንዲሁም በንብረት ላይ ጉዳት ሊያደርስ የሚችል የበካይ ነገሮች መጠንን፣

ሐ) ከኢንዱስትሪ፣ ከአደገኛ ነገሮች፣ ከሃይል ማመንጫ፣ ከተሽከርካሪዎች፣ ከአውሮፕላን እና ከመሳሰሉት የሚመነጩ አየር የሚበክሉ የበካይ ነገሮች መጠንን የሚወስን ይሆናል፡፡

፬. የአንድ ነገር አደገኛ ደረጃ የሚወሰነው የነገሩን ዓይነት፣ መጠን፣ ያለበትን ቦታና የአየር ንብረት ሁኔታ ከግምት ውስጥ በማስገባት ይሆናል፡፡

፭. የፍሳሽ ለአካባቢ ተስማሚነት ደረጃ

ሀ) ወደ ውሃ ወይም ወደ መሬት የሚደፋውን፣ የሚለቀቀውን፣ የሚቀበረውን ወይም ወደ ፍሳሽ መስመር እንዲገባ የሚፈቀደውን ፍሳሽ፣



2. The authority shall regulate the implementation of environmental standards enacted by relevant federal government offices until the administration enacts its owen standards. Incase where there is no standards enacted by federal government offices, the authority shall regulate the implementation of environmental standards issued by the concerned international organizations.

6. *Quality standards*

1. As stated under articles 5 of these regulations, the Government shall determine quality standards based on the enumerated elements herewith.
   (a) Relevant water quality standards that might be used for human welfare, environmental protection and different services.
   (b) Air quality standards and quality standards of material released into air which is favorable to human health & life as well as the wellbeing and reproduction of animals & plants.
   (c) Standards for the quality of soil which helps to determine the type and amount of chemicals applied to the soil.
   (d) Standards for noise to determine the noise of industries, construction sites, motor vehicles, Airplane, various materials, commercial enterprises and other that can generate noise.
   (e) Standards for production & control of hazards waste.
   (f) Standards for the discharge of effluents into water bodies and sewage systems.
   (g) Standards for the amount of odor which is favorable to environmental welfare & human health.
2. Standards for the quality of water concerning quality of water that might be used to domestic purpose, industries, recreation & when necessary, for other functions too.
3. Air quality standards determined:-
   (a) Minimum Air quality standards which are necessary for the wellbeing and human health.
   (b) The amount of pollutant materials that causes harm to human life, health and wellbeing of animals and plants which may cause damage on the property.
   (c) The amount of air pollutant that generates form industries, hazardous material, power generation, motor vehicles, airplanes and the likes.
4. The standard of hazards things determined by considering its type, amount, the place where it exists and the ecosystem.
5. Standard for favorable effluents.
   (a) The allowed quality of water that can be released or discharged or damped in to water or ground.

ለ) በፍሳሽ መስመር ተሰብስቦ በፍሳሽ ማጣሪያ ጣቢያ ከተጣራ በኋላ ወደ ውሃ ወይም መሬት የሚለቀቀው ፍሳሽ፣

፯. <u>ፍሳሽን ወደ ፍሳሽ መስመር ስለመልቀቅ</u>

፩. ማንኛውም ፍሳሽ ወደ ፍሳሽ መስመር ለመልቀቅ የሚፈልግ ሰው በሕግ ስልጣን ከተሰጠው አካል ፈቃድ ካልተሰጠው በስተቀር የፍሳሽ መስመሩን መጠቀም አይችልም፣

፪. ከዚህ በታች የተዘረዘሩትን የፍሳሽ የጥራት ደረጃዎች የማያሟላ ፍሳሽ ወይም ሌላ ነገር ወደ ፍሳሽ መስመር መልቀቅ ወይም ማስገባት፣ እንዲለቀቅ ወይም እንዲገባ ማድረግ የተከለከለ ነው፡፡

ሀ) በፍሳሽ ማጣሪያ ጣቢያ ሊጣራ የማይችል ወይም የማጣሪያ ጣቢያውን ሥራ የሚያውክ ወይም በማጣራት ሂደት ላይ ችግር የሚፈጥር ፍሳሽ፣

ለ) ከፍሳሽ ማጣሪያ ጣቢያ ተጣርቶ የሚወጣውን ፍሳሽ የጥራት ደረጃ በመቀነስ ወይም በማጓደል በመንግሥት የወጣውን ደረጃ እንዳያሟላ ያደርጋል ተብሎ የሚገመት ፍሳሽ፣

ሐ) በራሱ ወይም ከሌላ ንጥረ ነገር ጋር በመዋሀድ መርዛማ ኬሚካል በማመንጨት በመስመር ጥገና ላይ በሚሰሩ ወይም ማንሆል ውስጥ ገብተው በሚሰሩ ሠራተኞች ላይ ጉዳት ያደርሳል ተብሎ የሚገመት ፍሳሽ፣

መ) በራሱ ወይም ከሌሎች ንጥረ ነገሮች ጋር በፍሳሽ መስመር ወይም በማጣሪያ ጣቢያ ወይም የተጣራው ፍሳሽ በሚለቀቅበት ውሃ እና አፈር ላይ ጉዳት ያደርሳል ተብሎ የሚገመት ፍሳሽ፣

ሠ) የፍሳሹ ሙቀት ፍሳሹ ከመስመሩ ጋር በሚገናኝበት ቦታ ላይ ሲለካ ከ፶ ዲግሪ ሴንቲግሬድ የበለጠ ፍሳሽ፣

ረ) የፍሳሹ ፒኤች ከ፭ ነጥብ ፭ ካነሰ ወይም ከ፲ ነጥብ ዜሮ የሚበልጥ ከሆነ፣

ሰ) በፍሳሽ መስመር ውስጥ የሚቀጣጠል ወይም የሚፈነዳ ወይም መርዛማ ወይም አደገኛ ጋዝ ወይም ትነት ያመነጫል ተብሎ የሚገመት

ሸ) ከ፩፻ ዲግሪ ሴንቲግሬድ በታች በሆነ ሙቀት ሊተኑ የሚችሉ ነገሮችን በውስጡ የያዘ ፍሳሽ፣

ቀ) ዘይት፣ ጮማ፣ የተቃጠለ የሞተር ዘይት ወይም ሳሙና ነክ የሆነ እና ሌሎች መስመሩን ሊዘጉ የሚችሉ ወይም ማጣሪያ ጣቢያው በትክክል እንዳይሰራ ሊያደርጉ የሚችሉ ነገሮች በውስጡ የያዘ ፍሳሽ፣

በ) እንደ ሽንኩርት እና ድንች፣ ልጣጭ፣ እንጨት፣ ጠጠር፣ አሸዋ፣ ጨርቅ፣ አጥንት ድንጋይ ወዘተ የመሳሰሉትን ጠጣር ነገሮች በውስጡ የያዘ ፍሳሽ፣

በህግ ሥልጣን የተሰጠው አካል የፍሳሽ መስመር ቅጥያ ለማከናወን በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ ፪ ስር ከተደነገገው በተጨማሪ ሌሎች ዝርዝር ቴክኒካዊ መስፈርቶችንና አስፈላጊ የሆኑ ሁኔታዎች ሊወስን ይችላል፡፡



(b) The amount of water released or discharged in to water or ground after being collected and distilled by the distillation center.

7. *Discharging effluents in to sewerage system*

1. Any person who wants to discharge effluents in to the sewerage system shall not use the sewerage unless licensed by the organs authorized by law.
2. It is prohibited to discharge or to put in to sewerage system effluents and other materials which fails complex effluents standard here with.

(a) Effluents which are difficult to filter in the filtering center or challenges the activities of the center or creates a problem when the filtration under way.

(b) when the effluent is believed to minimize the quality of water produced by the filtration center and against the standards issued by the government.

(c) When it is / presumed that it cause/ harm to workers who maintain the channel or manhole as a result of generations of hazards chemicals by its own or when mixed with other elements.

(d) When it is believed/presumed to endanger sewerage system of filtration center or water and air when the effluent discharged, by its own or mixed with other elements.

(e) When temperature of the effluent becomes over 50 degree measured at the meeting place of the effluent & the channel.

(f) When the PH of the effluent is below 5.5 or above 10.0.

(g) When it is believed to generate flammable, or explosive, or poisons or hazardous gas or vapor in the sewerage line.

(h) Effluents containing substances which evaporate below $100^{o}_{c}$.

(i) Effluents containing oil , fats, or soapy substance which may block the channel or that affect the filtration center from performing well.

(j) Effluents containing solid such as wastes of onion or potato, wood, Sand, textile, bone and stone.

3. In addition to the elements set for under sub-article 2 of this article, the organ authorized by law may determine other detailed technical requirements & necessary conditions in order to connect effluent channel.

፰. <u>አካባቢን መበከል የተከለከለ ስለመሆኑ፣</u>

፩. በዚህ ደንብ መሠረት ፈቃድ ካልተሰጠ በስተቀር ማንኛውም ሰው

ሀ) ለልዩ ልዩ አገልግሎት ከተወሰነው የጥራት ደረጃ ውጭ ውሃን በአገልግሎት ላይ ማዋል፣

ለ) አደገኛ ነገሮችን ፍሳሽ፣ ቆሻሻን፣ ደረቅ ቆሻሻን ወይም ማንኛውንም በካይ ነገር በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ ወደ ወንዝ ውሃ፣ ወደ ጎርፍ መውረጃ ቦይ መድፋት ወይም መልቀቅ ወይም እንዲለቀቅ ማድረግ፣

ሐ) ለአየር ከወጣለት የጥራት ደረጃ በላይ በካይ ነገሮች ወደ አየር መልቀቅ፣

መ) ለአፈር ከወጣለት የጥራት ደረጃ በላይ ማንኛውንም በካይ ነገር ወደ አፈር ውስጥ መጨመር ወይም መልቀቅ ወይም መድፋት ወይም መቅበር፣

ሠ) በደረጃ ከተወሰነው መጠን በላይ ድምፅ ማውጣት፣

ረ) የአደገኛ ነገሮችን አመራረትና የአያያዝ ደረጃና መመሪያ መጣስ ወይም መተላለፍ፣

ሰ) በደረጃ ከተወሰነው መጠን በላይ መጥፎ ሽታ እንዲኖር ማድረግ፣ አይቻልም፣

፪. ማንኛውም ሰው በይዞታው ላይ የተከማቹ ወይም የሚመረቱ ነገሮችን ወደ መንገድ፣ ወንዝ ወይም የጎርፍ መውረጃ ቦይ እንዳይገቡ ለመከላከል የሚያስችሉ አስፈላጊ የሆኑ ቅድመ ዝግጅቶችን የማድረግ ግዴታ አለበት።

፫. ባለስልጣኑ በግለሰቦች ቦታ ላይ የፈሰሰ ወይም የተከማቸ ነገር በዝናብ ተጠርጎ ወደ መንገድ፣ ወንዝ ወይም የጎርፍ መውረጃ ቦይ ይገባል ብሎ ባመነ ጊዜ በባለንብረቱ ወጪ አስፈላጊው መከላከያ ሥራ እንዲሰራ ሊያዝ ይችላል።

፱. <u>አደገኛ ነገሮች አመራረትና አያያዝ ሥራ ላይ ለመሰማራት ስለሚያስፈልግ የምስክር ወረቀት፡-</u>

፩. አደገኛ ነገሮችን ለማምረት፣ ለማሸግ፣ ለማከማቸት፣ ለማጓጓዝ፣ ወደ አስተዳደሩ ክልል ውስጥ ለማስገባት ወይም ወደ ውጭ አገር ለመላክ፣ ለመሸጥ ወይም ለመለወጥ ወይም የመሳሰሉትን ተግባሮች ለማከናወን የሚፈልግ ማንኛውም ሰው ከሚመለከተው የፌዴራሉ መንግሥት መሥሪያ ቤት ወይም ከአስተዳደሩ አግባብ ያለው አካል የተሰጠ የብቃት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት መያዝ አለበት።

፪. ማንኛውም ሰው በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ ፩ የተጠቀሰውን ማናቸውንም ተግባር በአስተዳደሩ ውስጥ ለማካሄድ ከመጀመሩ በፊት የተሰጠውን የብቃት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት ለባለሥልጣኑ በማቅረብ መመዝገብ አለበት። ዝርዝሩ ባለሥልጣኑ በሚያወጣው መመሪያ ይወሰናል።

፫. ባለሥልጣኑ በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ (፪) የቀረበለትን የምዝገባ ጥያቄ ሕጋዊነት መርምሮ ከተቀበለው አመልካቹን መዝግቦ የምዝገባ ምስክር ወረቀት ይሰጠዋል።

8. *Prohibition of Environmental pollution*

1. Unless permitted by these regulations, it is prohibited to:

   (a) Use water exceeding the limited quality standards for different activities.

   (b) Release or putting hazardous materials, effluents, or solid wastes or any pollutant materials directly or indirectly into rivers or sewerage.

   (c) Release pollutants into air exceeding the stetted air quality standards.

   (d) Release, put or damp any pollutant materials into soil beyond the set standards of the soil.

   (e) Release noises exceeding the limited standards.

   (f) Violate or transcend standards & directive for the production & control of hazardous materials.

   (g) Made bad odor available above the limited standards.

2. Every one shall take the necessary prior preparation to prevent the flow of materials stored & produced in his possession in to passages, rivers and sewerage channels.

3. The authority may order the performance of necessary preventive measures to be taken by the owner when it believed that materials released or stored in once possession entered to passages, rivers or sewerage channels.

9. *Permit required to engage in the production and management of hazardous material.*

1. Every one who wants to perform the production, packing, storing, transporting, importing to the City or exporting, selling or exchange of hazardous materials shall have certificate of competency from the relevant/concerned federal government office or organ of the city.

2. Every one shall present and register his certificate of competency before the authority prior to his engagement in the city to any of the activities listed in sub-article 1 of this article.

3. The authority after evaluating the legality of the request of application of registration based on sub-article 2 of this article shall register & give certificate of registration when accepted.

፬. በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ ፩ በተደነገገው በማናቸውም ተግባር ደህ ደንብ ከመዕደቁ በፊት የተሰማራ ማንኛውም ሰው ደንቡ በፀደቀ በስድስት ወራት ጊዜ ውስጥ ከባለሥልጣኑ የብቃት ምስክር ወረቀት ማግኘትና መመዝገብ አለበት፡፡

፲. <u>መረጃ የመስጠት ግዴታ</u>

፩. በሥራው ጠባይ ምክንያት፡-

ሀ) ፍሳሽ ወይም ደረቅ ቆሻሻ ወይም ሌላ ማንኛውንም አደገኛ ነገር ወደ ውሃ የሚደፋ ወይም የሚለቅ ማንኛውም ሰው የተለቀቀ ውን ወይም የደፋውን ፍሳሽ ወይም ደረቅ ቆሻሻ ወይም አደገኛ ነገር ዓይነት፣ መጠንና ይዘት፣

ለ) በካይ ነገሮችን ወደ አየር የሚለቅ ማንኛውንም ሰው የበካይ ነገሮችን ዓይነት፣ መጠንና ይዘት፣

ሐ) ፍሳሽ ወይም ደረቅ ቆሻሻ ወይም ሌላ ማንኛውንም አደገኛ ነገር ወደ አፈር ውስጥ የሚደፋ ወይም የሚጨምር ወይም የሚቀብር ማንኛውም ሰው የተደፋውን፣ የተለቀቀውን፣ የተጨመረውን ወይም የተቀበረውን ፍሳሽ ወይም ደረቅ ቆሻሻ ወይም ሌላ ማናቸውም አደገኛ ነገር ዓይነት፣ መጠንና ይዘት፣

መ) ከተወሰነው መጠን በላይ ድምጽ የሚያመነጭ ማንኛውም ሰው ስለድምጹ መጠንና ሊያስከትል ስለሚችለው ተጽእኖ፣

ሠ) በምንም ምክንያት ይሁን ሽታ እንዲፈጠር ወይም እንዲኖር ያደረገ ማንኛውም ሰው ስለሽታው ምንጭና ይዘት፣ ሳይዘገይ ለባለ ሥልጣኑ ሪፖርት የማድረግ ግዴታ አለበት፡፡ ዝርዝሩ ባለሥልጣኑ በሚያወጣው የአሠራ ርና የቁጥጥር መመሪያ መሠረት ይወሰናል፡፡

፪. ባለሥልጣኑ አስፈላጊ በሆነ ጊዜ ሁሉ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ ፩ የተዘረዘሩት መፈጸማቸውን በተጠራጠረ ጊዜ በራሱ አነሳሽነት የመጠየቅና መረጃ የማግኘት መብት አለው፡፡

፫. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ ፩ እና ፪ መሠረት ለባለሥልጣኑ መረጃ የሚሰጥ ማንኛውም ሰው የሰጠው መረጃ የተሟላና ትክክለኛ ስለመሆኑ የማረጋገጥ ኃላፊነት አለበት፡፡

፬. ባለሥልጣኑ ከሚመለከታቸው ጋር በመተባበርና ይህን ደንብ ሳይቃረን በካዮች ተገቢው ቴክኖሎጂ ወይም አሠራር በመከተል ወይም ሌላ አማራጭ በመውሰድ በአካባቢ ላይ የሚያደርሱት ብክለት እንዲቀንስ ወይም እንዲወገድ ወይም ሙሉ በሙሉ እንዲቆም መወሰን ይችላል፡፡

፲፩. <u>ስለአካባቢ ቤተ ሙከራ</u>

፩. ባለሥልጣኑ ከአካባቢ ጥበቃና ብክለት ቁጥጥር አንፃር ያለበትን ሃላፊነት ለመወጣት እንዲችል በዚህ ደንብ መሠረት የአካባቢ ቤተ ሙከራ ያደራጃል፡፡

፪. በአካባቢ ቤተ ሙከራ ምርመራ ተደርጎ የተደረ ሰበት ሙያዊ የትንተና ውጤት በሕግ ፊት ተቀባይነት ያለው ይሆናል፡፡ ውጤቱ አጠራጣሪ መሆኑን የሚያስረዱ ተቀባይነት ያላቸው ምክንያቶች ሲቀርቡ ግን ምርመራው እንደገና እንዲካሄድ ሥልጣን ባለው የአስተዳደር ወይም የፍትህ ውሳኔ ሰጪ አካል ሊታዘዝ ይችላል፡፡

፫. የአካባቢ ቤተ ሙከራን የምርመራ ውጤት ምርመራ እንዲካሄድባቸው ከተፈቀዱ ጉዳዮች ውጭ እና ይህንኑ ውጤት መሠረት በማድረግ ውሳኔ ለመስጠት ሥልጣን ከተሰጣቸው የአስተዳደር ወይም የፍትህ አካሎች ውጭ ማቅረብ ወይም መጠቀም አይፈቀድም፡፡

፲፪. <u>ስለ አካባቢ ተቆጣጣሪ</u>

፩. ባለሥልጣኑ የዚህን ደንብ ድንጋጌዎች ለማስ ፈፀም ለሥራው ባስፈለገው መጠን ብቃት ያለው የአካባቢ ተቆጣጣሪ (ከዚህ በኋላ "ተቆጣጣሪ") ተብሎ የሚጠራ ይሰይማል ፡፡

4. Every person engaged in any of the activities listed in sub-article 1 of this article, prior to the issuance of these regulations shall have certificate of competency & registration certificate with in six months of the issuance of these regulations.

*10. Duty to provide information*

1. Everyone shall report to the authority immediately as a result of nature of his activities,
   (a) The amount type and content of effluents or solid wastes or hazardous materials released or allowed to get in to water.
   (b) The type, amount and volume of pollutant materials released in to air.
   (c) The type, amount & volume of the released dumped or buried effluents, solid wastes or any hazardous materials in the soil.
   (d) The frequency & impact of noises generated above the limit of noise.
   (e) Source & volume of odor created or existed by any reasons.

   The details shall be determined by a directive issued by the authority for implementation and control.
2. The authority when necessary has a right to request information by its own initiative when it doubts the performance of those activities listed under sub-article 1 of this article.
3. Every one who provides information to the authority as per sub article 1 & 2 of this article, shall be responsible to certify its comprehensiveness and correctness.
4. Without contradicting these regulations, the authority in cooperation with other concerned bodies may decide to minimize or to avoid or to stop pollution results from failure to adopt appropriate technology or method or other alternatives.

*11. Environmental Laboratory*

1. The authority shall establish environmental laboratory based on these regulations in order to discharge its responsibilities in view of environmental protection and pollution control and able to give professional witness.
2. The result of professional explanation achieved by a research in the laboratory shall be acceptable before the law. Where the situation justifies to do so, attributing to reasonable doubt, the competent government authority or the court may order repetition of the laboratory test.
3. It is prohibited to use or bring environmental laboratory reports other than the allowed function or administrative or judicial organs authorized to render decision based on it.

*12. Environmental Inspector*

1. The authority shall assign the necessary & qualified environmental Inspector here in after called Inspector, in order to execute the provisions of these regulations.

7

፪. ባለሥልጣኑ እያንዳንዱ ተቆጣጣሪ ፣ ተቆጣጣሪ ሆኖ መሰየሙን የሚያስረዳ የመታወቂያ ወረቀት ይሰጠዋል ። ተቆጣጣሪውም በሥራ ላይ ባለበትና በተጠየቀ ጊዜ የመታወቂያ ወረቀቱን መያዝ እና ማሳየት አለበት።

፫. ተቆጣጣሪው የዚህን ደንብ ዓላማዎች ፣ መርሆዎች እና ድንጋጌዎች በሥራ ለመተርጎም የሚያስችሉትን ሁኔታዎች ሁሉ ባለሥልጣኑ የማሟላት ኃላፊነት አለበት።

፬. የዚህን ደንብ ድንጋጌዎች አፈጻጸም በመከተል ማንኛውም ሰው የሚከተሉትን የመፈጸም ግዴታ አለበት ፤

ሀ) በደንቡ መሠረት ተቆጣጣሪው ተግባሩን ለማከናወን የሚያስፈልጉት ናሙናዎች ወይም ሰነዶችና ሌሎች አግባብነት ያላቸው መረጃዎች ሲጠይቀው የመስጠት ወይም የማቅረብ፣

ለ) ተቆጣጣሪው ደንቡን ለማስፈፀም የሚሰጠውን ማንኛውንም ትዕዛዝ የማክበርና የመፈፀም ፣

ሐ) ተቆጣጣሪው ሥራውን በሚያከናውንበት ጊዜ ያለማወክ ፣

፲፫. ስለአካባቢ ተቆጣጣሪ ሥልጣንና ተግባር፣

ተቆጣጣሪው የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባራት ይኖሩታል፡-

ሀ) በደንብ መሠረት የተመዘገቡ እና ፈቃድ ያገኙ ነገሮች ሥፍራዎችን፣ ህንፃዎችን፣ ፋብሪካዎችን፣ ተቋማትን፣ ኢንዱስትሪዎችን፣ ፋብሪካዎችን ወይም ተሽከርካሪዎችን የመፈተሽ፣

ለ) ፈቃዶች ፣ መዝገቦች ፣ ሰነዶች ፣ ወይም ሌሎች ነገሮች እንዲቀርቡለት ለመጠየቅ ወይም እነዚህኑ ለመቆጣጠር፣ ለመመርመር ወይም ቅጂ ለመውሰድ ፣

ሐ) የዚህን ደንብ ድንጋጌዎች ተግባራዊነት ለማረጋገጥ ምርመራዎችንና ቁጥጥሮች የማድረግ ፣

መ) አግባብነት ያላቸው ነገሮች ወይም ቁሶች ናሙና የመውሰድ ፣ ናሙናውን ለላብራቶሪ ምርመራ ወይም ትንተና የመላክ ፣

ሠ) የዚህ ደንብ ድንጋጌዎች በሚመለከታቸው የኢንዱስትሪ ፣ የፋብሪካ ፣ የንግድ ወይም ሌሎች ተቋሞች አካባቢን ይበክላሉ የሚል ግምት ሲኖር በቦታው ተገኝቶ ቁጥጥር የማድረግ ፣

ረ) የዚህን ደንብ ድንጋጌዎች ለመፈጸምና ለማረጋገጥ የሚያስፈልጉ ሌሎች ቁጥጥሮችን የማከናወን ።

ሰ) የዚህን ደንብ ድንጋጌዎች ተላልፏል ብሎ ያመነበትን ሰው ለጥያቄ ወደ ባለሥልጣኑ እንዲመጣ መጥሪያ የመስጠት ፤

ሸ) የአካባቢ ደረጃዎችና ተዛማጅ ግዴታዎች በሥራ ላይ መዋላቸውን የማረጋገጥ ።

፪. የዚህ ደንብ ድንጋጌዎች በመተላለፍ በአካባቢ ላይ ጉዳት አድርሰዋል ብሎ ሲያምን ተቆጣጣሪው ማንኛውንም ተሽከርካሪ ፣ የማምረቻ መሣሪያ ፣ ዕቃዎች ወይም ሌሎች ነገሮች ሊይዝ ወይም እንዲያዙ ሊያደርግ ይችላል።

2. The authority shall issue an identity card for each inspector showing that one is assigned. The inspector shall have the identity card with him and show it when requested.
3. The authority shall be responsible to fulfill conditions which help the Inspector to execute the objectives, principles and provision of these regulations in to effect.
4. In view of the execution of the provisions of these regulations, every one shall have the duty to perform the following obligations.
   (a) To provide or to bring before the inspector samples, documents and other relevant information's which are necessary to the inspector to perform his activity in accordance with the regulation.
   (b) To respect and perform any order given by the inspector in order to execute the regulation.
   (c) Not to disturb the inspector when discharging his duty.

13. *Power and duties of environmental Inspector.*

The Inspector shall have the following power and duties;

1. Any time and without the need to show court order;
   (a) To search places, buildings, institutions, industries, factories or motor vehicles registered and permitted in accordance with these regulations.
   (b) To require permits files, documents or other things or to regulate, investigate or to have a copy of these
   (c) To perform investigation & regulation as to the execution of the provisions of these regulations.
   (d) To collect samples from relevant things or objects and send them to laboratory investigation or analysis.
   (e) To regulate at the scene when it is believed that those industries, factories, trade or other institutions which shall observe these regulations pollute the environment.
   (f) To perform other regulatory activities in order to assure & execute the provisions of these regulations.
   (g) To send a notice to a person to appear before him for request when it is believed that he has person violates the provisions of these regulations.
   (h) To assure the application of environmental standards and related obligation in to effect.
2. The Inspector may seize or cause to be seized any motor vehicle, production Instruments, objects or other things when he believed that they damage the environment by violating the provisions of these regulations.

፫. ተቆጣጣሪው የዚህን ደንብ ድንጋጌዎች በመተላለፍ አካባቢን የበከለ ወይም አካባቢን ሊበክል መሆኑ የተደረሰበት ማንኛውንም ድርጊት እንዲቆም ለማድረግ ይችላል ። ድርጊቱ ተቋሙን የሚያዘጋ ከሆነ በጽሑፍ ውሳኔ የሚሰጠው ባለሥልጣኑ ይሆናል ። ባለሥልጣኑ የሚሰጠው ተቋሙን የመዝጋት ውሳኔ ተቋሙ የሚዘጋበትን ጊዜ መግለጽ አለበት ።

፬. ተቆጣጣሪው የዚህን ደንብ ድንጋጌዎች በመተላለፍ በአካባቢ ላይ የደረሰው ወይም የሚደርሰው ብክለት የሚቆምበትን ሁኔታ በተመለከተ የማሻሻያ ማስታወቂያ ለማምረቻ ተቋሙ ወይም ለድርጊቱ ፈጻሚ ሰው ለመስጠት ወይም አዲስ መሣሪያ ወይም የደህንነት መጠበቂያዎች በተወሰነ ጊዜ ውስጥ እንዲተከል ወይም እንዲቋቋሙ ለማዘዝ ይችላል።

ክፍል ሦስት

ስለ አካባቢ ብክለት ቁጥጥር ፣ ፈቃድና አስተዳደር

፲፬. ጠቅላላ

፩. የአካባቢ ብክለት ቁጥጥር ፈቃድ በዚህ ደንብ ከዚህ በኋላ "ፈቃድ" የሚሰጠው ወይም የሚታገደው ወይም የሚከለከለው ወይም የሚሠረዘው ማንኛውም ሰው በአካባቢ ላይ ሊያደርስ የሚችለውን ብክለት ለመቀነስ ወይም ለማስወገድ ወይም ለመቆጣጠር ወይም ለብክለቱ መንስዔ የሆነው እንቅስቃሴ ወይም ተግባር እንዲቆም ለማስቻል ነው።

፪. በዚህ ደንብ መሠረት ፈቃድ እንዲይዝ የሚጠየቀው የተቋቋመበት ዓላማ ወይም የሥራ እንቅስቃሴ ወይም ድርጊት በአካባቢ ላይ ብክለትን እንዲሁም በሰው ልጅ አኗኗር፣ጤንነት እና ደህንነት ላይ ምክንያት አሉታዊ ተፅዕኖ የሚያስከትል ማንኛውም ሰው ነው።

፫. የፈቃድ አሰጣጥ በባለሥልጣኑ የሚከናወን ይሆናል። ባለሥልጣኑ ስለተሰጠ ፈቃድ ትክክለኛና የተሟላ መረጃ የመያዝ ኃላፊነት አለበት።

፬. ፈቃድ የሚሰጠው ፣ የሚታደሰውና ታግዶ ከሆነ ዕገዳው የሚነሳው በካዩ ያደረሰውን ብክለት በራሱ ወጭ የማስተካከልና የመካስ ኃላፊነት አለበት የሚለውን መርህ በመከተል የአገልግሎት ክፍያ በመክፈል ይሆናል ።

፭. የፈቃድ አገልግሎት ክፍያ መጠን በባለሥልጣኑ ተጠንቶ በከተማው ካቢኔ ይወሰናል።

፲፭. ፈቃድ ለመስጠት ስለሚያበቁ ሁኔታዎች

፩. ባለሥልጣኑ ከዚህ በታች በተመለከቱት ሁኔታዎች መሠረት ፈቃዱን ይሰጣል።

ሀ) ሥራው ወይም ተግባሩ አዲስ እና የሚመለከተው ከሆነ የአካባቢ ተጽእኖ ግምገማ ሪፖርት ሲቀርብ ፣

ለ) እንደየአግባቡ ለአካባቢ አስቸኳይ ሁኔታ አስተዳደር የተዘጋጀ ዕቅድ ከነማስፈጸሚያው ስልት ሲቀርብ ፣

ሐ) ፈቃድ ጠያቂው በአካባቢ ላይ ሊያደርስ ለሚችለው ብክለት የማስወገጃ ወይም የመከላከያ ወይም የመቀነሻ ርምጃዎች ለመውሰድ ፈቃደኛ ሲሆንና ግዴታ ሲገባ ፣

3. The inspector may take measures to give up any activities which pollute or can pollute the environment by violating the provisions of these regulations. When the activity requires the closing of the institution, the authority shall decide in writing. The decision of the authority shall explain the time when the institution is closed.

4. The inspector may send adjustment notice to production institution or to a person to give up activities that pollute or may pollute the environment by violating the provisions of these regulations or order them to plant a new machinery or safety measures with in a certain period of time.

*Part Three*

*Environmental pollution, control permit & administration*

*14. General*

1. Environmental pollution control permit, here after refered as permit can be permitted, or suspended or prohibited or cancelled in order to minimize, avoid or regulate everyone who might pollute the environment or to stop the activities or function which causes pollution.
2. Any person required to have the permit when the objective of its establishment or job activities or function pollute the environment or causes the negative consequences on the livelihood, health or well being of human beings.
3. The authority is vested with the power to give the permit. It shall be responsible to have correct and comprehensive information as to the permit granted.
4. A permit shall be given or renewed and a suspension be canceled up on the payment of compensation by the pollutant for the damage he caused to the environment based on the principle "same shall pay the compensation."
5. Service charge for the permit shall be determined by the cabinet of the city

*15. Conditions to grant permit*

1. The authority shall give the permit based on the conditions herewith.
   (a) On submission of Environmental Impact assessment report for new jobs or activities/functions which shall required to present Environmental Impact Assessment report.
   (b) When necessary, submission of the Emergency plan & its implementation strategy for the management of Environment.
   (c) When the applicant is willing to eliminate, protect or minimize the possible pollution of the environment and enter to an obligation to that effect.

መ) በባለሥልጣኑ ሲጠየቅ ተጨማሪ ማስረጃ ዎችን ሲያቀርብ ፣

ሠ) አግባብነት ያላቸው ወገኖች ፈቃድ እንዲሰጥ የሚሰጡትን አስተያየት በማመዛዘን ፣

፪. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) /ሠ/ የተ መለከቱት ወገኖች ወይም አግባብነት ያላቸው የአካባቢው ነዋሪዎች ፣ መንግሥታዊ እና መንግሥታዊ ያልሆኑ መ/ቤቶች ስለሚወከሉበት ሁኔታ ባለሥልጣኑ በሚያወጣው መመሪያ ይወሰናል ።

፫. ፈቃድ እንዲሰጠው ያመለከተ ማንኛውም ሰው ጉዳዩ ሲታይ ቀርቦ ለባለሥልጣኑ የማስረዳት መብት አለው። በባለሥልጣኑ ከተጠየቀ ቀርቦ የማስረዳት ግዴታ አለበት ።

፬. የፈቃድ ጥያቄው ፍሳሽን ወደ ውሃ ሀብት ለመልቀቅ የሚቀርብ ሲሆን የሚከተሉት ከግምት ውስጥ መግባት አለባቸው።

ሀ) በውሃው ወይም በሌሎች ሀብቶች ጥራት እና ደህንነት ላይ ሊከተል ስለሚችለው አሉታዊ ውጤት ፣

ለ) አስቀድሞ የተሰጡት ተመሳሳይ ፍቃዶች ፣ በተ መሳሳይ የውሃ ሀብት ወይም ሌሎች ተያያዥ ሀብቶች ላይ ያላቸው አሉታዊ ተጽእኖ ፣

ሐ) ፈቃድ በተጠየቀበት የውሃ ሀብት ላይ የውሃ ፍላጎት ያላቸው የውሃ ተጠቃሚዎች ላይ ሊያስከትል የሚችለው አሉታዊ ተፅእኖ ፣

፭. የፈቃድ ጥያቄው ትነትን ወይም ጭስን /በካይ ነገር/ ወደ አየር ለመልቀቅ የቀረበ ሲሆን የሚከተሉት ሁኔታዎች ከግምት ውስጥ መግባት አለባቸው።

ሀ) በአካባቢ የአየር ጥራት ላይ ሊያስከትል ስለሚችለው አሉታዊ ውጤት ፣

ለ) አስቀድሞ የተሰጡ ፈቃዶች በአካባቢው አየር ላይ ያላቸው ወይም ያሳደሩት ተጽእኖ ፣

ሐ) በአካባቢው ያሉ ነዋሪዎች ፣ ኢንዱስትሪዎች ወይም የንግድ እንቅስቃሴዎች ፍላጎቶች ፣

፲፮. <u>የፈቃድ ማመልከቻ እና መረጃዎች አቀራረብ ሥርዓት</u>

፩. ባለሥልጣኑ ለእያንዳንዱ ፈቃድ ሊሰጥበት ለሚገባው ጉዳይ ራሱን የቻለ የማመልከቻ ቅጽ ያዘጋጃል ።

፪. ማንኛውም ሰው ፈቃድ ለማግኘት ባለሥልጣኑ ባዘጋጀው ለጉዳዩ አግባብነት ባለው ሠንጠረዥ የተመለከተውን የማመልከቻ ቅጽ በመሙላት ለባለሥልጣኑ ያቀርባል ።

፫. በዚህ ደንብ መሠረት ፈቃድ እንዲሰጠው የሚጠይቅ ማንኛውም ሰው እንደሚጠይቀው የፈቃድ ዓይነት ፣ ሊያሟላ የሚገባው ሁኔታና ሊያቀርብ የሚገባው መሠረታዊ መረጃ እንደ ተጠበቀ ሆኖ ከሚያቀርበው ማመልከቻ ጋር ፣

ሀ) ኢትዮጵያዊ ከሆነ ተገቢው የኢንቨስትመንት ፈቃድ ፣

ለ) የቅርብ ጊዜ /ሁለት/ ጉርድ ተመሳሳይ ፎቶ ግራፍ ፣

ሐ) የውጭ አገር ዜጋ ከሆነ የኢንቨስትመንት ፈቃድና የመኖሪያ ፈቃድ ፣



(d) Present other additional documents when required by the authority.

(e) Evaluating the suggestion to grant the permit of other relevant parties

2. The authority shall determine by a directive as to the representation of local community, governmental and non-governmental organizations and relevant parties indicated in sub-article 1/E/ of this article.

3. Any applicant for the permit has a right to appear and explain to the authority on the date assigned to here his case: when required by the authority to do so, the applicant shall have the obligation to appear and explain before him.

4. When the request of the permit is to discharge effluent to water resources, the following shall be taken in to consideration.

(a) Its negative impact on the quality & safety of water and other resources.

(b) The negative impact of prior permits over similar water resources and other related resources.

(c) The negative impact over those who have interest over the water which is subject to the permit requested

5. When the permit request is to discharge vapor or smokes/pollutant/ in to air, the following conditions shall be taken in to consideration.

(a) Its negative impact/over the Environmental air quality.

(b) Impacts of prior permits over the Environment.

(c) The interest/of the community, industries or trade activities in that locality.

*16. Application and Information of permit procedure.*

1. The authority shall prepare the formal for each activities that requires permit.
2. Any person who apply for permit shall fill and return to the authority the relevant form indicated in the schedule.
3. without prejudice to the type, condition and information expected from each applicant, any applicant for permit under these regulations in addition shall present;

(a) Investment permit/for Ethiopian Applicant.

(b) Two partial identical recent photos

(c) Investment and resident permit for foreigners

መ) አመልካቹ ማህበር ከሆነ እንደ አግባብነቱ፣
፩. የምዝገባ ምስክር ወረቀት ፣
፪. የማህበሩ የመመስረቻ ጽሑፍና የመተዳደሪያ ደንብ ፣
፫. የማህበሩ የበላይ ኃላፊ የቅርብ ጊዜ ሁለት ጉርድ ተመሳሳይ ፎቶ ግራፍ መያያዝ አለበት ።

ሠ) አመልካቹ የመንግሥት ተቋም ወይም የልማት ድርጅት ከሆነ ፣
፩. ተቋሙ የተቋቋመበት የማቋቋሚያ ሕግ፣ እና
፪. የተቋሙ የበላይ ኃላፊ የቅርብ ጊዜ ሁለት ጉርድ ተመሳሳይ ፎቶ ግራፍ መያያዝ አለበት ።

## ፲፯. ፈቃዱን ስለመስጠት ወይም ስለመከልከል

፩. ባለሥልጣኑ በዚህ ደንብ አንቀጽ ፲፮ መሠረት የቀረበለትን የፈቃድ መጠየቂያ ማመልከቻና መረጃዎች እንዲሁም በዚህ ደንብ አንቀጽ ፲፭ የተመለከቱትን ሁኔታዎች ከገመገመ በኋላ ፈቃዱ ሊሰጥ የሚገባው መሆኑ ሲያረጋግጥ እና ሲወስን ማመልከቻ በቀረበ በ ፲፭ ቀናት ውስጥ ፈቃዱን ለአመልካቹ ይሰጣል ።

፪. ባለሥልጣኑ በዚህ ደንብ አንቀጽ ፲፮ እና አንቀጽ ፲፭ መሠረት የቀረበለትን የፈቃድ መጠየቂያ ማመልከቻ ፣ መረጃዎች እና ሁኔታዎች ሲገመግም ያልተሟሉ ጉዳዮች ካጋጠሙት ይህንኑ እንዲያሟላ ማመልከቻው በቀረበ በ፲ ቀናት ውስጥ ለአመልካቹ በጽሑፍ ይገልጽለታል ።

፫. ባለሥልጣኑ ያቀረበለትን ማመልከቻ በዚህ ደንብ አንቀጽ ፲፮ እና ፲፭ መሠረት መረጃዎችን እና ሁኔታዎችን ከገመገመ በኋላ ጥያቄውን ያልተቀበለው እንደሆነ ያልተቀበለበትንና ፈቃዱን የከለከለበትን ምክንያት በመግለጽ ለአመልካቹ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ ፩ በተጠቀሰው ጊዜ ውስጥ በጽሑፍ ያሳውቃል።

## ፲፰. ስለፈቃዱ ጊዜና ዕድሳት

፩. ፈቃዱ ጸንቶ የሚቆየው ለአንድ ዓመት ብቻ ይሆናል ።

፪. የተሰጠው ፈቃድ በየዓመቱ መታደስ አለበት።

፫. ፈቃዱ እንዲታደስለት የሚጠይቅ ባለፈቃድ አመልካች እንደ አግባቡ የአካባቢ ተቆጣጣሪውን ሪፖርት ከማመልከቻው ጋር አያይዞ እንዲያቀርብ ሊጠየቅ ይችላል ።

፬. የፈቃዱ እድሣት ሊከለከል የሚችልባቸውን ዝርዝር ሁኔታዎች ባለሥልጣኑ በመመሪያ ይወስናል ።

፭. ፈቃዱ ሲታደስ የአገልግሎት ክፍያ በባለ ፈቃዱ ይከፈላል ።

## ፲፱. ፈቃድ ስለማገድ

፩. ፈቃዱ የተሰጠው ማንኛውም ሰው ፣
ሀ) ፈቃዱ ከተሰጠበት ሁኔታ አንጻር ሊሟሉ የሚገባቸውን ሁኔታዎች አሟልቶ ያልተገኘ እንደሆነ፣

(d) If the applicant is an Association: its shall present.
1. Registration certificate
2. Memorandum and article of Association.
3. Two partial identical recent photos of the head of the Association

(e) For governmental and non-governmental applicants:
1. Establishment Law and
2. Two partial identical recent photos of the head of the institution.

*17. Power to grant or reject permit*

1. The authority shall grant the permit with in 15 days commencing from the date of receipt of the request,
Where the authority recognizes & decides to give the permit after the evaluation of the application & information pursuant to article 16 as well as the conditions under article 15 of these regulations.
2. The authority shall inform the applicant in writing within 10 days un fullfilled conditions and information which the authority discovered while evaluating the application as per article 15 & 16 of these regulations.
3. The authority shall inform in writing the applicant the rejection of the application with in the period stated in sub-article 1 of this article, where it finds the documents un acceptable in evaluating pursuant to the conditions and information provided in article 15 and 16 of these regulations.

*18. Duration & Renewal of permit*

1. The permit remains valid for a year.
2. The permit shall be renewed every year.
3. The applicant for renewal of a permit may be requested to submit the report of the environmental inspector together with the application.
4. The authority shall determine the detailed conditions for rejection or renewal of permit through directives.
5. The permit holder shall pay service fee for renewal.

*19. Suspension of permit*

1. A permit can be suspended where the holder:
(a) Fails to fulfill the conditions expected of him.

ለ) ባለሥልጣኑ የሚጠይቃቸውን መረጃዎች በወቅቱና በትክክል አሟልቶ ያልተገኘ እንደሆነ ፣

ሐ) በማንኛውም ሌላ ሁኔታ ይህን ደንብ ወይም ደንቡን ለማስፈጸም የወጣውን መመሪያ የጣሰ እንደሆነ ባለሥልጣኑ ጉድለቶቹ እስኪስተካከሉ ፈቃዱን አግዶ ማቆየት ይችላል ።

፪. ፈቃዱ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) መሠረት ሲታገድ ባለሥልጣኑ ፈቃድ የታገደበትን ምክንያትና በተወሰነ ጊዜ ውስጥ ባለፈቃዱ ጉድለቶቹን ለማስተካከል ሊወስድ ስለሚገባው እርምጃ ለባለፈቃዱ በጽሁፍ ያስታውቃል።

፫. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ /፪/ መሠረት የጽሁፍ ማስታወቂያ የደረሰው ባለፈቃድ በማስታወቂያው በተወሰነው ጊዜ ውስጥ ጉድለቶቹን የማስተካከል ግዴታ አለበት።

፳. <u>ፈቃድ ስለመሰረዝ</u>

፩. በዚህ ደንብ መሠረት ፈቃድ የተሰጠው ማንኛውም ሰው በባለሥልጣኑ በአንቀጽ ፲፯ መሠረት ፍቃዱን የሚሰርዘው፣

ሀ) ፈቃዱ የተሰጠው ወይም የታደሰው የሀሰት ወይም የተጭበረበረ መረጃ በማቅረብ ወይም በሕገ-ወጥ መንገድ መሆኑን ሲያረጋግጥ፣

ለ) ፈቃዱ የተሰጠበትን ሥራ ያቆመ እንደሆነ ወይም ፈቃዱ የተሰጠበት አላማ ያበቃ እንደሆነ፣

ሐ) ፈቃዱ ሲታገድ ፈቃዱ የታገደበትን ሁኔታ በአንቀጽ ፲፱ መሠረት በወቅቱ ያላሟላ እንደሆነ፣

መ) ተደጋጋሚ የፈቃድ ዕገዳ ጥፋቶች የፈጸመ እንደሆነ፣ ባለሥልጣኑ በዚህ ደንብ አንቀፅ ፲፯ መሠረት የተሰጠውን ፈቃድ ይሰርዛል።

፪. ባለሥልጣኑ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀፅ (፩) በተገለፁት ምክንያቶች ፈቃድ የመሰረዝ ውሳኔ ከመስጠቱ በፊት ባለፈቃዱን በደብዳቤ ጠርቶ ስለጉዳዩ ሀሳቡን በጽሁፍ እንዲያቀርብ ያደርጋል። ማስጠንቀቂያው የደረሰው ባለፈቃድ ማስጠንቀቂያው በደረሰው በ፴ ቀናት ውስጥ ስለጉዳዩ ያለውን ሃሳብ በጽሁፍ ለባለሥልጣኑ ለማቅረብ ይችላል።

፫. ባለፈቃዱ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፪) መሠረት ሃሳቡን ካላቀረበ ወይም ቢያቀርብም ምክንያቱ በቂ ሆኖ ካልተገኘ ባለሥልጣኑ ፈቃዱን ለዘለቄታው ይሰርዛል።



(b) Fails to provide correct & timely information when requested by the authority.

(c) In any circumstance violates these regulations and other directives issued to the effective implementation of these regulations until corrective measures are introduced.

2. When the authority suspends the permit as per sub-article 1 of this article, it shall provide written notice to the permit holder about the reasons of the suspension and the corrective or adjustment measures to be taken within a certain time.

3. A permit holder who receives the written notice as per sub-article 2 of this article, shall take the adjustment or corrective measures with the specified time.

*20. Cancellation of permit.*

1. The authority shall cancel the permit as per article 17 of these regulations;

   (a) Where the permit or renewal were granted as result of mischief, forgery, falsified information or illegal ways;

   (b) Where the activities or the objective for the permit ceased.

   (c) In case of suspension failure of the permit holder to take timely corrective or adjustment measures as per article 19 of these regulations,

   (d) Where the permit holder performs cause of suspension activities repetitively.

2. The authority, before rendering decision of cancellation of permit as per sub-article 1 of this article, shall notify the permit holder and receive his written opinion. The permit holder who receives a notice may provide the authority his written opinion about the issue within 30 days.

3. The authority permanently cancels the permit where the permit holder fails to provide its opinion or provides insufficient reasons as per sub-article 2 of this article.

## ክፍል አራት

## ስለ ልዩ ልዩ ኃላፊነቶች

### ፳፩. ስለ አስተዳደራዊ ውሳኔዎች እና ይግባኝ

፩. ባለሥልጣኑ በቀጥታ ወይም በተቆጣጣሪዎች አማካኝነት የአካባቢ ብክለት እንዳይኖር ወይም ብክለት የሚያስከትል ተግባር እንዳይጀምር ወይም እንዳይቀጥል ወይም የአካባቢ ብክለት የሚያስከትለው ድርጊት እንዲቆም ወይም የአካባቢ ብክለት የሚያስከትለው ወይም ሊያስከትል የሚችለው አደገኛ ነገር እንዳይመረት ወይም እንዳይንቀሳቀስ ወይም እንዲወገድ ወይም በጥንቃቄ እንዲያዝ በማንኛውም ሰው ላይ ውሳኔ ለመስጠት ወይም የቁጥጥር እርምጃ ለመውሰድ ሥልጣን አለው፡፡

፪. በማናቸውም የባለሥልጣኑ አካል በተወሰነ ውሳኔ ወይም በተወሰደ እርምጃ ቅር የተሰኘ ማንኛውም ሰው ውሳኔውን ወይም እርምጃውን ተግባራዊ አድርጎ ውሳኔው በተሰጠው በ፲ ቀናት ውስጥ ለባለሥልጣኑ ሥራ አስኪያጅ ይግባኙን ለማቅረብ ይችላል፡፡

፫. ለባለሥልጣኑ ሥራ አስኪያጅ የቀረበለትን የይግባኝ ማመልከቻ ከመረመረ በኋላ ውሳኔውን ወይም የተወሰደውን እርምጃ በማጽናት፣ በማሻሻል ወይም ውድቅ በማድረግ በ፲፭ የሥራ ቀናት ውስጥ ውሳኔ ለመስጠት ይችላል፡፡

፬. ውሳኔው ወይም የቁጥጥር እርምጃው የዚህን ደንብ ድንጋጌዎች አፈጻጸም ያልተከተለ ሆኖ ሲገኝ ባለሥልጣኑ በዚህ ምክንያት በተበዳዩ ላይ ለደረሰው ጉዳት ተጠያቂ ይሆናል፡፡

፭. የባለሥልጣኑ ሥራ አስኪያጅ ውሳኔ የመጨረሻ ይሆናል፡፡ ሆኖም በተሰጠው ውሳኔ ላይ ቅሬታ ያለው ወገን ጉዳዩን ሥልጣን ባለው ፍ/ቤት እንዲታይለት ሊያቀርብ ይችላል፡፡

### ፳፪. ስለ ፍትሐብሔር ኃላፊነት

፩. ማንኛውም ሰው የዚህን ደንብ ድንጋጌዎች በመተላለፍ ወይም በመጣስ በአካባቢ ላይ ለሚያደርሰው ብክለት እና/ወይም በሰዎች ደህንነት፣ አኗኗር እና ቁሳዊ ጥቅሞች ላይ በብክለቱ ምክንያት ለሚያደርሰው ጉዳት እንደቅደም ተከተሉ፡-

ሀ) አካባቢውን ከብክለቱ በፊት ወደነበረበት ሁኔታ በራሱ ወጪ የመመለስ፣ እና/ወይም

ለ) በሰዎች ወይም በጥቅሞቻቸው ላይ ብክለቱ ያደረሰውን ጉዳት የመካስ ፣ ኃላፊነት አለበት፡፡

፪. ከአካባቢ ብክለት ጋር የተገናኘ ጉዳይ የቀረበለት የፍትህ ተቋም ዋናውን የኃላፊነት ጥያቄ እልባት ከመስጠቱ በፊት፣ የብክለቱን ድርጊት በካዩ እንዳይጀምር ወይም እንዳይቀጥል ወይም ብክለት ያስከተለው ድርጊት እንዲቆም ትዕዛዝ ለመስጠት ይችላል፡፡

## PART-FOUR

## *Liabilities*

### 21. *Administrative decisions and Appeal*

1. The authority is authorized to decide or take regulatory measures against any person directly or through its inspectors to avoid the very existence or beginning or continuity of environmental pollution or to stop activities that may cause pollution or to stop the production and transportation of hazardous materials or to avoid & hold them carefully.

2. Any person dissatisfied by the decision or measure taken by the body or the authority shall per-form it and may appeal to the general manager of the authority within 10 days commencing from the date so he notified.

3. The general manager of the authority after evaluating the appeal may up hold or amend or reject decision or measures taken within 15 days.

4. The authority shall be responsible for the damage sustained by the appellant as a result of the decision or measures taken against the provisions of these regulations.

5. The decision of the general manager shall be final. However, any person dissatisfied by the decision may take the case to the court having jurisdiction.

### 22. *Civil liability*

1. Any person who transcends or violate the provision of these regulations shall be liable for the pollution of the environment and/or for damages sustained over the well being, life and material as a result of pollution in its order of priority.

   a) To reinstate the environment to its former or original situation by his cost.

   b) To compensate damages caused on persons and their interest as a result of pollution.

2. The judiciary, before determining the liability, on the case brought before it, may order suspension or injection order over the activities that causes pollution.

፳፫. <u>ስለወንጀል ኃላፊነት</u>

የዚህ ደንብ ድንጋጌዎች የተላለፈ ማንኛውም ሰው አግባብ ባለው የፌዴራል መንግሥት ሕግ ወይም ወንጀለኛ መቅጫ ሕግ መሠረት ይቀጣል፡፡

፳፬. <u>ከአካባቢ ተቆጣጣሪዎች ጋር በተገናኘ ስለሚፈጸሙ ጥፋቶች</u>

፩. የሚከተሉትን ድርጊቶች የፈጸመ ማንኛውም ሰው ጥፋተኛ ነው፣

ሀ) ተቆጣጣሪው በዚህ ደንብ መሠረት ግዴታውን እንዳይፈጽም ማጓተት ወይም ማወክ፣

ለ) በዚህ ደንብ መሠረት ተቆጣጣሪው የሚሰጠውን የዚህን ደንብ ድንጋጌዎች የተላለፈ ማንኛውም ሰው አግባብ ባለው የፌዴራል መንግሥት ሕግ ወይም ወንጀለኛ መቅጫ ሕግ መሠረት ማናቸውንም ሕጋዊ ትዕዛዝ ወይም አስፈላጊ ሁኔታ አለመፈፀም፣

ሐ) ይህ ደንብ በሚፈቅደው መሠረት ተቆጣጣሪው ወደ ሥፍራው ወይም ወደ ቅጥር ግቢው ወይም ወደ ሕንፃው እንዳይገባ መከልከል፣ ወይም ፈቃድ ያገኙ ተቋማት፣ ኢንዱስትሪዎችን፣ ፋብሪካዎችን እና ተሽከርካሪዎችን እንዳይፈትሽ ማድረግ፣

መ) በተቆጣጣሪ ሲያያቸው የሚፈልጋቸውን መዛግብት ወይም ሌሎች ነገሮችን ለማሳየት ፈቃደኛ ሆኖ አለመገኘት፣

ሠ) በዚህ ደንብ መሠረት ማንነቱንና አድራሻውን እንዲገልጽ በተቆጣጣሪው ሲጠየቅ አለመናገር ወይም የተሳሳተ ስምና አድራሻ መንገር፣

ረ) ተቆጣጣሪውን ማሳሳት ወይም ለተቆጣጣሪው የተሳሳተ መረጃ መስጠት፣

ሰ) በዚህ ደንብ መሠረት በተቆጣጣሪው የተሰጠን የማሻሻያ ትእዛዝ አለመፈፀም፣

፪. በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀጽ (፩) የተመለከቱትን ጥፋቶች የፈፀመ ማንኛውም ሰው አግባብነት ባለው ሕግ መሠረት ይቀጣል፡፡

፳፭. <u>ከመዝገብ አያያዝ ጋር የተገናኙ ጥፋቶች</u>

፩. ማንኛውም ሰው፡-

ሀ) ስለሚያካሂደው ሥራ እንቅስቃሴ፣ ምርት ተረፈ ምርትና በምርት ሂደቱ ስለሚፈጠረው ቆሻሻ አያያዝ አወጋገድ ሁኔታ የሚገልጽ መዝገብ ወይም መረጃ ካልያዘ፣

ለ) ማናቸውንም መረጃ በተጭበረበረ ሁኔታ ከቀየረ፣ በዚህ ደንብ መሠረት ጥፋተኛ ነው፡፡

፪. በዚህ አንቀፅ በንዑስ አንቀፅ ፩ የተመለከቱትን ጥፋቶች የፈፀመ ማንኛውም ሰው አግባብነት ባለው ሕግ መሠረት ይቀጣል፡፡



23. *Criminal liability*

Any person who violates the provisions of these regulations shall be punished by the relevant federal laws or penal code.

24. *Offenses relating to environmental Inspectors.*

1. Any person shall be liable when he/she commits either of the following offences.

   a) cause delaines or became an obstacle to the inspector while discharging his obligation under these regulations.

   b) Failure to comply with any law full order or necessary requirements of the inspector as per these regulations.

   c) Refuse an inspector entry in to any and or premise or in to buildings or refuse the search permitted institutions, industries, factories or motor vehicles as per these regulations.

   d) Become unwilling or hinders record or other things which the Inspector requires.

   e) Withhold or mislead his identity address when requested by the Inspector as per these regulations.

   f) Mislead or provide the Inspector with wrong information.

   g) Failure to comply with the adjustment measures proposed by the inspector as per these regulations.

2. Any person who commits any offences under sub-article 1 of this article, shall be punished by the relevant federal laws.

25. *Offences relating to record*

1. Any person who committees an offence pursuant to these regulations, when he/she

   a) Fails to hold record & information's as to the activities, production, wastes, and control & holding of wastes produced in the production process.

   b) Alters any information.

2. Any person committees any of the offences listed in sub-article 1 of this article shall be punished by the relevant laws.

፳፮. <u>ከአደገኛ ነገሮች ጋር በተገናኘ ስለሚፈፀሙ ጥፋቶች</u>

፩. የሚከተሉትን ድርጊቶች የፈፀመ ማንኛውም ሰው ጥፋተኛ ነው፡-

ሀ) አደገኛና ጎጂ ቁሶችን፣ የምርት ሂደትንና ቆሻሻ በአግባቡ አለመያዝ፣

ለ) ስለቆሻሻው ወይም ኬሚካሉ ወይም አደገኛ ሂደት ሌሎች ቁሶች ምንነት እያወቀ የተሳሳተ ነገር መፃፍ፣

ሐ) ስለቆሻሻው ፣ ስለኬሚካሉ ወይም አደገኛ ድርጊት ወይም ነገር መረጃ መደበቅ ወይም መከልከል፣

መ) ለሕገወጥ የቆሻሻ ወይም የኬሚካል ወይም አደገኛ ድርጊት ወይም እንቅስቃሴ መተባበር፣

፪. ከዚህ በላይ በንዑስ አንቀፅ /1/ የተመለከቱትን ጥፋቶች የፈፀመ ማንኛውም ሰው በፌዴራል መንግሥት ለዚሁ ጥፋት አግባብነት ባለው ሕግ መሠረት ይቀጣል።

፳፯. <u>አቤቱታ የማቅረብ መብት</u>

፩. ነገሩ የሚመለከተው መሆኑን ማስረዳት ሳይጠበቅበት፣ ማንኛውም ሰው በአካባቢ ላይ ጉዳት አድርሷል ወይም ጉዳት ሊያስከትል የሚችል ተግባር እየፈፀመ ነው በሚለው በማን ኛውም ሰው ላይ ለባለሥልጣኑ መረጃ የመስጠት ወይም አቤቱታ የማቅረብ መብት አለው።

፪. ባለሥልጣኑ በሰላሳ ቀናት ውስጥ ለቀረበው መረጃ ወይም አቤቱታ ውሳኔ ካልሰጠ ወይም አቤቱታ አቅራቢው በውሳኔው ካልተስማማ፣ ውሳ ኔው ከተሰጠበት ወይም የሚሰጥበት የጊዜ ገደብ ካለፈበት አንስቶ በስድሳ ቀናት ውስጥ ሥልጣን ላለው ፍርድ ቤት ክስ መመሥረት ይችላል።

## <u>ክፍል አምስት</u>

### <u>ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች</u>

፳፰. <u>ስለማበረታቻ</u>

ብክለት ለመከላከል ወይም መጠኑን ለመቀነስ በሚያስችል ዘዴ መጠቀም ለሚጀምር ለማንኛውም ነባር ድርጅት የሚሰጥ ማበረታቻ የአካባቢ ብክለት ቁጥጥር አዋጅ ቁጥር ፫፻/፲፱፻፺፬ን ለማስፈፀም በፌዴራል መንግሥት በሚወጣው ደንብ አግባብ ይወሰናል።

፳፱. <u>ስለአካባቢ አስቸኳይ ጉዳዮች</u>

፩. ከፍተኛ እና አደገኛ የአካባቢ ብክለት በመድረሱ ወይም ለመድረስ ተቃርቧል የሚያሰኝ በቂ ምክንያት ሲኖረው ባለሥልጣኑ ከአስተዳደሩ ጋር በመመካከር አስቸኳይ ሁኔታው ለሕዝብ እንዲገለፅ የማድረግ ግዴታ አለበት።

፪. ማንኛውም ሰው በሚያካሂደው የሥራ እንቅስቃሴም ይሁን በተቋሙ የሥራ ባህርይ ወይም አደገኛ ነገሮች ምክንያት ከፍተኛና አደገኛ የአካባቢ ብክለት ሊከተል ቢችል ይህንኑ ለመከላከል፣ ለማስወገድ፣ ለመቀነስ፣ ወይም ለማሻሻል የሚያስችል የአደጋ ጊዜ ዕቅድ ሊኖረው ይገባል። የዕቅዱም ብቃት እንዲገመገም በየጊዜው ለባለሥልጣኑ ማቅረብ አለበት።

26. *Offenses relating to hazardous material.*

1. Any person shall be liable if he commits the following offences

   a) Fails to hold hazardous or chemicals or harmful objects, production process & wastes properly

   b) Knowing about wastes or chemicals or nature of harmful activities but acts the contrary.

   c) Fails to provide or prohibit information as to wastes, chemicals, harmful things or activities.

   d) Cooperates with illegal activities or wastes, or chemical or harmful things or activities.

2. Any person who commits offences listed in sub-article 1 shall be punished by the relevant federal law

27. *Right to long complaint*

1. Any person shall have the right to provide information or to lodge a complaint to the authority against any person allegedly causing actual or potential or potential damage to the environment, without the need to show any vested interest.

2. When the authority fails to give a decision to the information or the complaint within thirty days or when the person who has lodged the complaint is dissatisfied with the decision, he may institute a court case with in sixty days form the date the decision has been given or the deadline for decision has elapsed.

## PART FIVE

### *Miscellaneous provisions*

28. *Incentives*

Incentives for the introduction or methods in to an existing undertaking that enable to prevent or minimize pollution shall be determined by the regulation to be issued by the Federal government for the implementation of Environmental pollution control proclamation No. 300/2002.

29. *Environmental Emergency Matters.*

1. The authority in consolation with the administration shall disclose the emergency matter to the public when it has a good-cause showing that high and serious environmental pollution materialized or to be materialized.

2. Any person, as a result of activities he performed as well as nature of the work or hazardous things which may cause high and series environmental pollution, shall have a plan for the emergency time which helps to protect, avoid, minimize or adjust the pollution and submit the plan timely to the authority for evaluation.

፫. ማንኛውም ሰው በሚያካሂደው የሥራ እንቅስቃሴ ባህርይ ወይም በተቋሙ የሥራ ባህርይ ወይም በኃላፊነት በሚያዛቸው አደገኛ ነገሮች ምክንያት ከፍተኛና አደገኛ የአካባቢ ብክለት ሲደርስ ወይም መድረሱ ሲገመት ለባለሥልጣኑ ወዲያውኑ የማስታወቅ ግዴታ አለበት፡፡

፬. ማንኛውም ሰው ከፍተኛና አደገኛ የአካባቢ ብክለት በመድረሱ ምክንያት የዚህኑ ውጤት ለማገድ፣ ለመከላከል፣ ለማሻሻል ወይም ባለሥልጣኑ ለሚያደርገው ማናቸውም የአስቸኳይ ጊዜ ጥረቶች የመተግበር እና አቅሙ በፈቀደ መጠን የመሳተፍ ግዴታ አለበት፡፡

፭. በአካባቢያዊ አስቸኳይ ክስተት ወቅት ባለሥልጣኑ ወይም ተቆጣጣሪው አደጋውን ወይም የአደጋውን ውጤት ለመከላከል፣ ለመቆጣጠር፣ ወይም ለማሻሻል ከዚህ በታች የተመለከቱትን መፈፀም ይችላል፡፡

ሀ) ወደማናቸውም ሥፍራዎች፣ ቤቶች፣ ተቋሞች፣ ሕንፃዎች ያለፍርድ ቤት ትዕዛዝ በማናቸውም ሰዓት ለመግባት፣

ለ) በማናቸውም ሥፍራዎች ወይም ተቋሞች ውስጥ በአካባቢ ላይ የደረሰውን አደጋ ለመከላከል የሚረዳ ማናቸውንም ስትራክቸር ወይም ማሽነሪ፣ ወይም ማቴሪያል ለመገንባት ወይም ለመትከል፣

ሐ) በካዩን ነገር ወይም በበካዩ ነገር ሊጠቁ ይችላሉ ተብሎ የሚገመቱትን ማናቸውንም ነገሮች፣ ዕፅዋት ወይም እንስሳት ወደማናቸውም የአካባቢ ክፍል ለማግለል፣

መ) ማናቸውንም ተሽከርካሪ ለማስቆም፣ ለመመርመር ወይም ለመፈተሽ ወይም ይዞ ለማቆየት፣

፮. ባለሥልጣኑ ከዚህ በላይ ስለተገለጹት የአካባቢ አስቸኳይ ጉዳዮች ሲያጋጥሙ ሊወሰዱ ስለሚገባቸው ቴክኒካዊ፣ አስተዳደራዊና የፀጥታ እርምጃዎች ፣ የአስቸኳይ ጊዜ ዕቅድና አተገባበር የቅንጅት ጉዳዮች በተመለከተ ዝርዝር መመሪያ ያወጣል፡፡ በዚሁ መመሪያ መሠረት ከሚመለከታቸው ጋር ሁሉ በመተባበር ተግባሩን ያከናውናል፡፡

፴. <u>ከአጎራባች ክልሎች ጋር ተባብሮ ስለመሥራት</u>

፩. ባለሥልጣኑ በአስተዳደሩ ውስጥ የሚከሰቱ ወይም ሊከሰቱ የሚችሉ የአካባቢ ብክለቶች ውጤቶቻቸው እንዳይዛመቱ ለመከላከል ወይም ለመቀነስ እንዲቻል ከሚመለከታቸው አጎራባች የክልል መስተዳድሮች ጋር በመተባበር ይሰራል፡፡

፪. ባለሥልጣኑ ከሚመለከታቸው የክልል መስተዳድሮች ጋር ከአካባቢ ብክለት ጋር በተገናኘ ሁኔታ የአካባቢ ጥበቃ ምክር ቤት ከአስተዳደሩ ካቢኔ ጋር በመመካከር ይወስናል፡፡ ያመቻቻል ፡፡ ባለሥልጣኑም ይተገብራል፡፡

፫. ባለሥልጣኑ ትብብር እንዲደረግባቸው በተወሰኑ የትብብር መስኮች ረገድ የተደረጉ ጥረቶች የተደረሰባቸውን ውጤቶች በተመለከተ ለአካባቢ ጥበቃ ምክር ቤት እና ለአስተዳደሩ የከንቲባ ጽ/ቤት ወይም ካቢኔ ሪፖርት ያቀርባል፡፡

3. Any person shall report immediately to the authority when high & serious environmental pollution materialize or to be materialized as a result of nature of its activity or nature of the institution or as a result of hazardous materials under his control.

4. Any person shall cooperate & take part for effort made to block, prevent or adjust by the authority in emergency matters when high & seviour environmental pollution materializes.

5. The authority or the inspector, in case of environmental emergency matters, may take measures to prevent, control or adjust the damage through;

   a) To enter at any time with out the need to show court order in to any places, homes, institution, buildings.

   b) To plant & construct machineries and other structure of any place or within institution to protect damages on the environment.

   c) To transfer objects, plants or animals which may be affected by the pollution.

   d) To stop or suspend, investigate and search any vehicles

6. The authority will issue regulation addressing environmental emergency situations and technical, administrative and security measures to be used as well as plan & its implementation. The authority in collaboration with the concerned body shall carry out its activity.

30. *Cooperation with neighboring Region.*

1. The authority shall take measures to protect or minimize environmental pollution and its effect from transmitting to other places together with neighboring regions.

2. The environmental pollution control council and the city cabinet shall determine areas and conditions of cooperation with neighboring regions and the authority shall implement the decision

3. The authority shall report to environmental protection council and the mayor office or cabinet efforts and results achieved in cooperation to the environmental pollutions control council.

፴፩. ስለመተባበር

ለዚህ ደንብ አፈፃፀም ማንኛውም ሰው የመተባበር ግዴታ አለበት፡፡

፴፪. የመሸጋገሪያ ድንጋጌ

የዚህ ደንብ አፈፃፀም የሚመለከተው ማንኛውም ሰው ይህ ደንብ ከፀናበት ጊዜ ጀምሮ በአሥራ ሁለት ወራት ውስጥ የሚያስፈልጉ መረጃዎችንና ሁኔታዎችን ሁሉ በማማሟላት ከባለሥልጣኑ የአካባቢ ብክለት ቁጥጥር ፈቃድ ማግኘት አለበት፡፡

፴፫. ደንቡ ከሌሎች ህጎች ጋር ስላለው ግንኙነት

፩. ይህን ደንብ የሚቃረን ማንኛውም ደንብ መመሪያ ወይም ልማዳዊ አሠራር ደንቡ በሚሸፍናቸው ጉዳዮች ላይ ተፈፃሚነት አይኖረውም፡፡

፪. በዚህ ደንብ ያልተሸፈኑ ጉዳዮች በፌዴራል የአካባቢ ብክለት ቁጥጥር አዋጅ ቁጥር ፫፻/፲፱፻፺፬ ድንጋጌዎች መሠረት ተፈፃሚ ይሆናል፡፡

፴፬. ደንቡ ስለሚፀናበት ጊዜ

ይህ ደንብ ከሚያዝያ ፳፮ ቀን ፲፱፻፺፰ ዓ.ም. ጀምሮ የፀና ይሆናል፡፡

አዲስ አበባ

ሚያዝያ ፳፮ ቀን ፲፱፻፺፰ ዓ.ም.

የአዲስ አበባ ከተማ ጊዜያዊ አስተዳደር



31. *Duty to cooperate*

Any person shall have the duty to cooperate in the implementation of these regulations.

32. *Transitional Provisions.*

Any person who is subjecte to these regulations shall have a permit from the authority within 12 months from the date of entry in to force of these regulations after fulfilling the necessary information & conditions.

33. *Relationship between the regulation & Other laws.*

1. Any regulation, directives or customary practices inconsistent with these regulations shall not be applicable regarding maters provided there in.
2. Matters uncovered by these regulations shall be governed by the provisions of environmental pollution control proclamation No.-300/2002.

34. *Effective date*

These regulations shall come into force as of May 4, 2006.

Done at Addis Ababa .

This 4th day of May 2006